**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

| | | |
|---|---|---|
| 1ki Diro Kiiro 8<br>Hawaasa, Arfaasa 1, 2013 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaale Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፰<br>ሀዋሳ፣ ጥር ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም |



**Amado**

**Wodhote Kiiro 8/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Investimentete Komishiine Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho …… Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፰/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኮሚሽንን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ……. ገጽ ….**


## WODHOTE KIIRO 8/2013

### Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Investimentete Komishiine Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho

Sidaamu dagoomu qoqqowi miinju latishshi rahisatenna qoqqowu teessaano heeshshote deerra woyyeessate investimente jawaachishanna halashsha hasiissinohura;

Qoqqowunita investimentete millimmo lossate, halashshatenna garunni massagate handaara aliidimmatenni gashshitanno bissa addintanni qoqqowunita jeefisiisaano bissa uurrisate,

## ደንብ ቁጥር ፰/፳፻፲፫

### የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት ኮሚሽንን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል የኢኮኖሚ ልማት ለማፋጠንና የክልሉን ነዋሪዎች የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ኢንቨስትመንትን ማበረታታትና ማስፋፋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የክልሉን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማሳደግ፤ ለማስፋፋት እና በአግባቡ ለመምራት ዘርፉን በበላይነት የሚያስተዳድሩ አካላትን በተለይም የክልሉን አስፈጻሚ አካላት ለማቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር




AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

biilloonyena loosu qeecha murate fulino lallawi kiiro 3/2012 quwa 10 (1)A garinni uurritino investmentete komishiine biilloonyenna loosu qeecha mura hasiissinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma jeefisiisaanote amaale mini qoqqowunita jeefisiisaano bissa uurrisate, biilloonyenna loosu qeecha murate fulino lallawi kiiro 3/2012 quwa 10(12) hunda uynoonnisi biilloonyi garinni tenne wodho fushshino.

**GAFA MITE**

**<u>XAPHOOMA WORO</u>**

**1. Ha'rancho Umo**

Tinne wodho "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Investmentete Komishiine Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fultino Wodho Kiiro 8/2013" yine woshshinara dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horosi garinni wole tiro aanoha ikka hoogiro tenne wodho giddo:

1. **"Qoqqowo"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
2. **"Investimente''** yaa haaro uurrinsha uurrisi'rate woy noo uurrinsha halashshate woy woyyeessate dureessu woxisinni woy danunni woy lamunkunni fushshanno

ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ አንቀጽ ፲(፩)ሀ መሠረት የተቋቋመውን የኢንቨስመንት ኮሚሽንን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት የክልሉን አስፈጻሚ አካላት ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር ፫/፳፻፲፪ አንቀጽ ፲ (፲፪) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

1 **አጭር ርዕስ**

ይህን ደንብ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፰/፳፻፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2 **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1 "ክልል" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡
2 "ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ወይንም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይንም ለማሻሻል በባለሀብት በገንዘብ ወይንም በአይነት ወይንም በሁለቱም

kapitaalete fulooti.

3. **“Investimentete baatto”** yaa quchumahonna baadiyyete investimentete owaantera bandoonni baattooti.
4. **“Borde’’** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma investimentete hajo aliidimmatenni ha’runsate tenne wodhonni uurrino bisooti.
5. **“Komite”** yaa Zoonete, Woradaho hattono Hawaasi quchumi gashshootinna woloottu quchumma gashshootira investimentete millimmo aliidimmatenni massagate tenne wodho garinni uurritino investimente jeefisiisate komiteeti.
6. **“Komishiine”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma investimentete komishiinenna taqqu taqqunni hedhannose tantano hanqafanno.
7. **“Investere”** yaa qoqqowu giddo investimentete fajjo adhe investe assino gobaydi woy giddo investereti.
8. **“Lekkishsha adha”** yaa qoqqowu giddo noo jeefisiisaano loosu uurrinshuwa uytannota investmentete ledo xaaddanno owaante mittu mereershira aate dandiinanni gede jeefisiisaano uurrinshuwanni dhaaddote riqiwo adhate.
9. **“Riqiwo”** yaa qoqqowu giddo noo jeefisiisaano uurrinshuwa uytanno investimentete ledo xaddanno owaante investere xa’midhanno woyte komishiinete ogeessi investere riqiwe

የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፡፡

3 "የኢንቨስትመንት መሬት" ማለት በከተማና በገጠር ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የተከለለ መሬት ነው፡፡

4 "ቦርድ" ማለት በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንቨስትመንት ጉዳይን በበላይነት ለመከታተል በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ አካል ነው፡፡

5 "ኮሚቴ" ማለት በዞኖች በወረዳዎች እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ አስተዳደርና ሌሎች ከተማ አስተዳደሮች የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን በበላይነት ለመምራት በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው፡፡

6 "ኮሚሽን" ማለት የክልሉ የኢንቨስትመንት ኮሚሽንና በየደረጃው የሚገኙ መዋቅሮቹን ያጠቃልላል፡፡

7 "ባለሀብት" ማለት በክልል ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመውሰድ ኢንቨስት ያደረገ የሀገር ውስጥ ወይም የውጪ ባለሀብት ነው፡፡

8 "ውክልና መውሰድ" ማለት ክልሉ ውስጥ ባሉ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የሚሰጡ ኢንቨስትመንት ነክ አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል መስጠት እንዲቻል ከመስሪያ ቤቶቹ በቀጥታ ውክልና መውሰድ ነው፡፡

9 "መተካት" ማለት ክልሉ ውስጥ ባሉ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የሚሰጡና ከኢንቨስትመንት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን

aanno jeefisate owaanteeti.

**3. Jeefishshu Mami-geeshsha**

Tini wodho qoqqowu investimentete komishiine biilloonyi hundaanni nooriranna konni garinni investimentete loosira milli yitannori aana jeefantanno.

**4. Koo-teemmate Xawishsha**

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni worroonnihu horosi garinni wole koo-teemmano hanqafannoho.

**GAFA LAME**

**INVESTIMENTETE KOMISHIINE LAINOHUNNI**

**5. Komishiinete Hexxo**

Komishiinete hexxo qoqqowoho xawashshonna lifixa investimentete gashshooti amuraate loosu aana hosiisatenni investimente jawaachishanna halashshate.

**6. Qara Loosu Mine**

Komishiinennihu qaru loosu mini Hawaasi quchumira ikkeenna hasiishshisi garinni woroonni heedhanno gashshootu taqquwa tantanamate dandiitanno.

**7. Komishiinete Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Komishiine:

1. Investimentete badantino baatto adhite

አገልግሎቶች ባለሀብቶች ሲጠይቁ የኮሚሽኑ ባለሙያ ባለሀብቱን ተክቶ የሚሰጠው የማስፈጸም አገልግሎት ነው፡፡

**3 የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስልጣን ስር በሆኑና በዚሁ አግባብ በሚንቀሳቀሱ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**4 የጾታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ በአንድ ፆታ የተገለጸው እንደ አግባብነቱ ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**ስለ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን**

**5 የኮሚሽኑ ዓላማ**

የኮሚሽኙ ዓላማ በክልሉ ግልጽና ቀልጣፋ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ስርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት እና ማስፋፋት ይሆናል፡፡

**6 ዋና መስሪያ ቤት**

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በሀዋሳ ከተማ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በተዋረድ ባሉ አስተዳደር እርከኖች ሊደራጅ ይችላል፡፡

**7 የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር**

ኮሚሽኑ፡-

1 ለኢንቨስትመንት የተለየ መሬት ተረክቦ

baattote maareekkora amaddanno; jeefisiisaano bissa amaale mini fajjiro wodho wonshitanno investerootira seeru garinni sayissanno;

2. Baadiyyete investimentete baatto la'annonsa bissa ledo waaxamatenni qixxeessitanno; sayisse aate doogo injeessitanno, bikkite investimentete wodho garinni investerete sayisse uytanno;
3. Qoqqowu giddo afantanno jiro kuusonna investimentete doorsha ikkitinori taje la'annonsa loosu sekiterenni gamba assitanno; fatiltanno; tuqissanno; investimentete pirojekituwa pirofayilla qixxeessitanno; egensiissanno;
4. Qoqqowu investimentete hajubba lainohunni mereershimmatenni soqqamatenni investimentete millimmo halashshitanno; jawaachishshanno; wolootu sekitere loosu minna ledo waaxamatenni seerunni fajjinoonni investimentete ledo xaaddanno owaante shiqqanno gara injeessitanno;
5. Uynoonni biilloonyi garinni investimentete xa'muwa shiqqanno woyte garimma noosi seeri garinni keente investimentete fajjo uytanno; haaroonsitanno; soorritanno; hooltanno;
6. Zoonete woy Hawaasi quchumi gashshootinni shiqqanno investimentete baatto fajjanto yitanno muro hedo

በመሬት ቋት ይይዛል፤ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ሲፈቀድ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ህግ መሠረት ያስተላልፋል፤

2 በገጠር የኢንቨስትመንት መሬት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ያዘጋጃል፣ የርክክብ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ለክቶ በኢንቨስትመንት ደንብ መሰረት ለባለሀብቶች ያስረክባል፤

3 በክልሉ ውስጥ የሚገኘው የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አማራጭ ዕድሎች መረጃ ከሚመለከታቸው ሴክተሮች ይሰበስባል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፕሮፋይሎችን ያዘጋጃል፤ ያስተዋውቃል፤

4 በክልሉ የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን በሚመለከት በማዕከልነት በማገልገል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ያስፋፋል፤ ያበረታታል፤ ከሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት በሕግ የተፈቀዱ ኢንቨስትመንት ነክ አገልግሎቶች የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

5 በተሰጠው የሥልጣን ክልል መሰረት የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ሲቀርቡ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በመገምገም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይለውጣል፤ ይሰርዛል፤

6 ከዞን ወይም ከሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የሚቀርብ የኢንቨስትመንት መሬት ይፈቀድ

garimma noose investimentete baatto sayse aate seeri garinni keente jeefisiisaano bissa amaale minira murote shiqishshanno;

7. Investerootu daafuro ajishate komishiine woloota loosu minnara uynanni investimentete ledo xaaddo noonsa owaante riqiwo adhatenni investerete mittu mereershi owaante uytanno;
8. Qoqqowoho investerete dancha investimentete qooxeessa kalaqate dandiissiissanno poolisenna gumulsiisate hayyo qixxeesitanno; garimma noosi bisinni fajiniro loosu aana hosiissanno;
9. Qoqqowoho investimente halashshatenna jawaachishate hattono qoqqowunniha dancha su'ma dhaawate kaa'litanno qajeelshuwa, borro, xawishshuwanna filmuwa, qixxeessitanno; tuqissanno; leellisho qixeesitanno; qixxaabbino labanno pirogiraamma beeqqitanno;
10. Garimma noonsa investimentete seerubba garinni investimentete bobbakkino investeroota fajjinoonninsa kakkayishshi horaameeyye ikkitanno gede assitanno;
11. Investimentete fajjo noonsa pirojekituwa jeefishsha ha'runsitanno; investimentete fajjo amaddino gadadonna qoosso ayirrisamansanna kakkayishshu hasi'noonni horora hosansa buuxxanno;
12. Investerootu taje, balaxotenna gedeni investimentete amaalenna tekinikete irko

የውሳኔ ሀሳብ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መሬት ማስተላለፍ ህግና መስፈርት መሰረት በመገምገም ለመስተዳድር ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፤

7 የኢንቨስተሮችን ውጣ ውረድ ለመቀነስ ኮሚሽኑ በሌሎች መስሪያ ቤቶች የሚሰጡ ከኢንቨስትመንት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎቶች በውክልና በመውሰድ እና ባለሀብቶችን በመተካት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣል፤

8 በክልሉ ለባለሀብቶች ምቹ የሆነ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር የሚያስችሉ የፖሊሲና የአፈጻጸም እርምጃዎችን ያመነጫል፤ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

9 በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት እንዲሁም የክልሉን መልካም ገጽታ ለመገንባት የሚረዱ ስልጠናዎችን፣ ጽሁፎችን፣ መግለጫዎችን እና ፊልሞችን ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፤ አውደ ርዕዮችን ያካሂዳል፤ በተዘጋጁ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ላይ ይሳተፋል፤

፲ አግባብ ባላቸው የኢንቨስትመንት ህጎች መሰረት በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች የተፈቀደላቸውን ማበረታቻዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፲፩ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያላቸው ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ይከታተላል፣ በኢንቨስትመንት ፈቃድ የተመለከቱ መብቶችና ግዴታዎች

owaante uytanno;

13. Gashshootu taqqara afantanno investimentete loosi minna kaajjishate kaa’litanno amaaletenna tekinikete irko uytanno; buusansiissanno; ha’runsitanno; gutu amaalamate battala qixxeessitanno; mixote jeefishshi ripoortenna mixo adhitanno; gamba assite la’annonsa bissara shiqishanno;
14. Investimente lainohunni qoqqowu deerrinni e’anno sheemaatubbanna woyyeessinonnire borreessite amadanno;
15. Qoqqowoho assinanni investimente aana xaaddanno sayikki bissa hi’ra eanna woloota mitiimma la’annonsa bissa ledo waaxamatenni seera agarino garinni tidhantanno gede assitanno;
16. Qoqqowu investimente kaajjishshanno yite ammantanno biddissuwa burqisse investimentete bordera shiqishshe wonsiisanno; loosu aana hossanno gede assitanno;
17. Loosu aana noo loosu amuraatenna seera woyyeessate dandiisiissanno hedo shiqishshanno;
18. Garunni latisa hoogate korkaatinni ittisatenna hoolate qaafo adhinanni investimentete pirojektubba aana investimentete wodho garinni seeru qaafo adhitanno; jeefishshano boordete egensiissanno;
19. Hasiishshisi garinni qoqqowu gobbaanni

መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪ ለባለሀብቶች የመረጃ፣ የቅድመና ድህረ ኢንቨስትመንት የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፫ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶችን ለማጠናከር የሚረዱ የምክርና የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ የጋራ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርትና ዕቅድ ይቀበላል፤ አጠናቅሮ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፲፬ ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በክልል ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶችንና ማሻሻያዎችን መዝግቦ ይይዛል፤

፲፭ በክልሉ በሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ላይ የሚከሰቱ የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነቶችንና ሌሎች ማነቆዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በህግ አግባብ እንዲፈቱ ያደርጋል፤

፲፮ የክልሉን ኢንቨስትመንት ያጠናክራሉ ብሎ ያመነባቸውን መመሪያዎች ቀርጾ ለኢንቨስትመንት ቦርድ በማቅረብ ያጸድቃል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤

፲፯ በሥራ ላይ ያለውን አሰራርና የሕግ ማዕቀፍ ለማሻሻል የሚያስችሉ ሀሳቦችን ያቀርባል፤

፲፰ በአግባቡ ባለማልማታቸው ምክንያት የስረዛና የዕገዳ እርምጃ የሚወሰድባቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ላይ

investimentete ha’runso borro mine fana dandiitanno;

20. Investimente jawaachishatenna halashshate kaa’lannoha wole assooteno assitanno.

**8. Komishiinete Tantano**

Komishiinete aante noo tantano heedhanose:

1. Mootimmatenni somantanno komishiinerenna hasiishshu garinni layinki komishiinere;
2. Loosoho hasiissanno loosaasine heedhannose.

**9. Komishiinerichu Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Komishiinete qara loosu jeefisiisaancho ikke seeru garinni komishiinete loossa massaganno; gashshanno;
2. Konni quwira cinaancho quwa 1 aana worroonniti xaphooma woro noo gede heedheenna qaru komishiinere:
   a) Tenne wodhora quwa 7 dirroonni komishiinete biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiissanno;
   b) Qoqqowu dagittete loosaasine seeri garinni komishiinete loosaasine gaamanno; gashshannonna geegiissanno;
   c) Komishiinete fajjinoonni baajeete loosu pirogramenna faynansete seeri garinni fulo assanno;

የኢንቨስትመንት ደንብን ተከትሎ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ አፈጻጸሙን ለቦርድ ያሳውቃል፤

፲፱እንደአስፈላጊነቱ ከክልሉ ውጪ የኢንቨስትመንት ላይዘን ጽሕፈት ቤት ሊከፍት ይችላል፤

፳ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል።

**8 የኮሚሽኑ አቋም**

ኮሚሽኑ ከዚህ በታች የተመለከተው አቋም ይኖረዋል፦

1 በመንግሥት የሚሾም ኮሚሽነርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች፤

2 ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል።

**9 የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር**

1 ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ በመሆን በህግ መሠረት የኮሚሽኑን ስራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ስልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤

ለ) በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች ህግ መሠረት የኮሚሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

d) Sayikki bissa ledo assinanni xaadooshshira komishiine riqiwanno;

e) Worosiinni noo tantano massagannonna qorqoranno;

f) Loosu bilchaantera hasiisanno deerrinni biilloonyisinna loosu qeechisi aaninni gama booce wolootu komishiinete losaasinera saysara dandaanno.

**10. Layinki Komishiinere Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Komishiinerichaho hundaancho ikke:

1. Komishiinete tantano garinni mitto handaara massaganno;
2. Komishiinerichu aano looso jeefisanno;
3. Komishiinerichu hee'ranokki woy loosara dandaannokki yannara riqiwe loosanno.

## GAFA SASE

## INVESTIMENTETE BORDE LAINOHUNNI

**11. Uurra**

Qoqqowunita investmentete hajo aliidimatenni massagganonna harunsitanno borde konni gedensanni "Borde" yine su'minanni bisi tenne wodhonni uurrino.

**12. Bordete Miillanna Borrote Mine**

1. Qoqqowu prezidaantichi woy

ሐ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደ በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

መ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ሠ) በስሩ ያሉ መዋቅሮችን ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

ረ) ለስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲ የምክትል ኮሚሽነር ተግባርና ኃላፊነት**

ተጠሪነት ለኮሚሽነሩ ሆኖ፡-

1 በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት አንድ ዘርፍ ይመራል፤

2 ከኮሚሽነሩ የሚሰጡ ተግባራትን ይፈጽማል፤

3 ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ ተክቶ ይሰራል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ኢንቨስትመንት ቦርድ

**፲፩ መቋቋም**

የክልሉን ኢንቨስትመንት ጉዳይ በበላይነት የሚመራና የሚከታተል ቦርድ ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ አካል በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

prezidaantichunni riqiwamannohu boordete sooreessaati;

2. Komishiinete qara komishiinere boordete borreessaanchonna miila ikkanno;
3. Kiironsa hasishshu garinni murranninna Prezidaantichunni riqiwantanno miilla heedhannose;
4. Bordete borro mini komishiineniwa ikkanno.

**13. Bordete Biiloonyenna Loosu Qeecha**

Borde:

1. Investimentete seerubba, wodhubbanna biddissuwa jeefishshanna komishiinete looso aliidimmatenni massagganno; qorqortanno; ha’runsitanno;
2. Tenne wodho jeefishshi ledo amadante ka’anno loosu gari hajubba aana gumulo uytanno;
3. Investimente loosu aana hoosiisate fultino wodho jeefisate hasiissanno biddissuwa fushshitanno;
4. Komishiinete, Zoonnatenna Hawaasi quchumi investimentete jeefisiissano komite uytanno gumulo aana koffi yitanno investere shiqishidhanno kadote koffeenya buuxatenni gumulo uytanno;
5. Komishiine uytanno owaantera baatisiissanno baatooshshi deerra murtanno;
6. Baxxino kakkayishsha afi’rate hasiisannonsa investimentete dannara

**፲፪ ስለቦርዱ አባላት እና ጽሕፈት ቤት**

1 የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም በርዕሰ መስተዳድሩ የሚወከል የቦርድ ሰብሳቢ፣

2 የኮሚሽኑ ኮሚሽነር የቦርዱ ጸሐፊና አባል፣

3 ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰኑና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል።

4 ኮሚሽኑ የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።

**፲፫ የቦርዱ ስልጣንና ተግባር**

ቦርዱ፡-

1 የኢንቨስትመንት ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች አፈጻጸምና የኮሚሽኑን ስራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣

2 ከዚህ ደንብ አፈጻጸም ጋር ተያይዘው የሚነሱ የአሰራር ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

3 ኢንቨስትመንትን ለመተግበር የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣

4 ኮሚሽኑ የዞን የሀዋሳ ከተማ የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኙ ባለሀብቶች የሚያቀርቡለትን ይግባኝ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፣

5 ኮሚሽኑ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚያስከፍለው የክፍያ መጠን ይወስናል፣

6 ልዩ ማበረታቻ ማግኘት ለሚገባቸው የኢንቨስትመንት አይነቶች መመሪያ ያወጣል፣

biddissa fushshitanno;

7. Woyyaabbino millimmo assatenni luphiima guma maarekkisiissano investerootira afansha uytanno;
8. Zoonnate, Woraddatenna Quchummate investimentete hossanno baatto qixxaabbanno gede buusansiissanno; luphi yitino gobboomunna qoqqowu horo noonsa investimentera hossara dandiitanno baatto qixxaabbannonna taje investimentete baatto maareekkora eo ikkite amadantanno gede assitanno;
9. Investimente lifixisate hasiissannori xintu latishshinna wolootu investmentete hasiissannori wo'mitanno gede buusansiissanno;
10. Investimente jawaachishatenna halashshate kaa'litanno woloota assoote assitanno.

**14. Bordete Gambooshshe**

1. Boorde ajay ajeenna sasu agani giddo mitte higge uurrinshu gambooshshe assitanno; hasiisiha ikkiro aye yannarano wiinamu gambooshshe assa dandiitanno.
2. Boordete miilla bocu aleenni leelturo gambooshshu guutaho.
3. Boordete gumulo huurotenni baxxitanno; huuro lamenkawa taalte gibburo, gambansaanchu aanno huuro hidhitanno.
4. Kuni quwi agaramino gedeenni hee'reenna boorde umise gambooshshu amuraati wodho fushshitara dandiitanno.



7 የተሻለ እንቅስቃሴ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ልማታዊ ባለሀብቶች እውቅና ይሰጣል።

8 በዞኖች፣ በወረዳዎች እና በከተሞች ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት እንዲዘጋጅ ያስተባብራል። የላቀ ሀገራዊና ክልላዊ ፋይዳ ላላቸው ኢንቨስትመንቶች ሊውል የሚችል መሬት እንዲዘጋጅና መረጃው በኢንቨስትመንት መሬት ቋት ገቢ ተደርጎ እንዲያዝ ያደርጋል።

9 ለኢንቨስትመንት መፋጠን የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችና ሌሎች አቅርቦቶች እንደሚሉ ያስተባብራል።

፲ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**፲፬ ስለቦርዱ ስብሰባ**

1 ቦርዱ ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2 ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3 የቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል። ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

4 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## GAFA SHOOLE

## INVESTIMENTE JEEFISIISSANO KOMITE LAINOHUNNI

### 15. Investimente Jeefisiissano Komite

1. Qoqqowu hundaanni heedhanno gashshootu taqqubara investimentete hajo aliidimmatenni harunsitanno investimente jeefisiissano komite konni gedensanni "Komite" yine su'minanni bissi tenne wodhonni uurrino.
2. Zoonetenna Hawaasi quchumi komite hundaanchimmansa boordetenna komishiinete ikkitanna woraddatenna quchumu gashshooti komite hundaanchimmansa zoonete investimentete komiteranna zoonete deerrinni investimentete hajo ha'runsitanno tantanora ikkitanno.

### 16. Komitete Miillanna Borrote Mine

1. Zoonete investimentete komite konni woroonni noo miilla heedhannose:
   - a) Qaru gashshaanchi gambansaancho ikkanno;
   - b) Zoonete deerinni investimentete hajo ha'runsitanno tantano massagaanchi borreessaanchonna miila ikkanno;
   - c) Qaru gashshaanchinni riqiwantanno miilla heedhanno; kiironsa hasiishshu garinni gumullanni.

## ክፍል አራት

## ስለ ኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ

### ፲፭ ስለኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ

1 ከክልል በታች በሚገኙ አስተዳደር እርከኖች የኢንቨስትመንት ጉዳይን በበላይነት የሚከታተል የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ አካል በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

2 የዞን እና የሀዋሳ ከተማ ኮሚቴ ተጠሪነት ለቦርዱ እና ለኮሚሽኑ ሲሆን የወረዳና የከተማ አስተዳደር ኮሚቴ ተጠሪነት ለዞን ኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴና በዞን ደረጃ የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን ለሚከታተል አደረጃጀት ይሆናል፡፡

### ፲፮ የኮሚቴ አባላት እና ጽሕፈት ቤት

1 የዞን ኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

- ሀ) የዞኑ ወይም የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ሰብሳቢ ይሆናል፤
- ለ) በዞን ደረጃ የኢንቨስትመንት ጉዳይ የሚከታተል አደረጃጀት አስተባባሪ አባልና ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤
- ሐ) በዋና አስተዳዳሪው የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

2. Hawaasi quchumi gashshooti investimentete jeefisiisaano komite aanino gari miilla heedhannose:
   a) Quchumu kantiiwi gambansaancho;
   b) Quchumu gashshooti investimentete borro mini sooreessi woy loosu ha'rinsho massagaanchi miilanna borreesaancho ikke loosanno;
   c) Quchumu kantiiwinni riqiwantanno miilla heedhanno; kiironsa hasiishshu garinni gumullanni.
3. Woradunna quchumu gashshooti investimentete gumulsiisaano komite miilla:
   a) Woradu gashshaanchi woy kantiiwu sooreessa ikkeenna wolootu miilla hasiishshu garinni qaru gashshaanchinni woy kantiiwunni su'mantanno.
   b) Woradu woy quchumu gashshooti investimentete yunite sooreessi miilanna borreessaancho ikkanno.
4. Gashshootu taqqubara heedhannonna investmentete hajo harunsitanno tantano komitete borrote mine ikkite horo uyitanno.

2 የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የከተማው ከንቲባ ሰብሳቢ፤
   ለ) የከተማ አስተዳደሩ የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም የሥራ ሂደት ባለቤት አባልና ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤
   ሐ) በከተማው ከንቲባ የሚወከሉ አባላት ይኖሩታል፤ ቁጥራቸው እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል፤
3 የወረዳና የከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፡-
   ሀ) የወረዳ አስተዳደሩ ወይም እንደአግባብነት ከንቲባ ሰብሳቢ ሆኖ ሌሎች አባላት እንደአስፈላጊነቱ በዋና አስተዳዳሪው ወይም በከንቲባው ይሰየማሉ፤
   ለ) የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ዩኒት ባለበት አስተባባሪው አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡
4 በየአስተዳደር እርከን የሚገኝ የኢንቨስትመንት ጉዳይ የሚከታተል መዋቅር የኮሚቴው ጽ/ቤት በመሆን ያገለግላል፡፡

### 17. Komitete Gambooshshe

1. Komite aganunni mitte higge uurrinshu gambooshshe assitanno; hasiisiro aye yannarano wiinamu gambooshshe assitara dandiitanno.

### ፲፯ ስለ ኮሚቴው ስብሰባ

1 ኮሚቴው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. Komitete miilla bocu aleenni leelturo gambooshshu guutaho.
3. Komitete gumulo huurotenni baxxitanno; huuro lamenkawa taalte gibburo, gambansaanchu aanno huuro hidhitanno.
4. Kuni quwi agaramino gedeenni hee’reenna komite umise gambooshshu amuraati wodho fushshitara dandiitanno.

**18. Komitete Biilloonyenna Loosu qeecha Komite:**

1. Investimentete seerubba jeefishshanna investimentete loossa aliidimmatenni massagganno; qorqortanno; ha’runsitanno;
2. Luphiima guma maareekkisiissino investerootira afansha uytanno;
3. Investimentete ikkitanno baatto qixxaabbanno gede assitanno;luphi yiino gobboomunna qoqqowu hornyi noonsa investimentootira ikkitara dandiitanno baatto qixxaabbanno gedenna taje investimentete maareekora amadantanno gede assitanno;
4. Investimetete wonsha hasiissannorenna wolootu shiqa hasiissannori wo’manno gede massagganno;
5. Investimentete pirojektuwa gumulate yannara xaaddanno qarrubba tiritanno; pirojektuwa investimentete seeri garinni irkissannonna jawaachishshanno;
6. Investimente jawaachishatenna

2 ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3 የኮሚቴው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

4 የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ውስጠ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፰ የኮሚቴው ስልጣንና ተግባር**

ኮሚቴው፡-

1 የኢንቨስትመንት ሕጎች አፈጻጸምንና የኢንቨስትመንት ስራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤

2 ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ልማታዊ ባለሀብቶች እውቅና ይሰጣል፤

3 ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ የላቀ ሀገራዊና ክልላዊ ፋይዳ ላላቸው ኢንቨስትመንቶች ሊውል የሚችል መሬት እንዲዘጋጅና መረጃው በኢንቨስትመንት መሬት ቋት እንዲያዝ ያደርጋል፤

4 ለኢንቨስትመንት የሚስፈልጉ መሰረተ ልማቶችና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሟሉ ያስተባብራል፤

5 በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ወቅት የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ይፈታል፤ ፕሮጀክቶችን በኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት ይደግፋል፤ ያበረታታል፤

halashshate kaa'litanno woloota ledote hajubba gumultanno;

7. Konni quwi cinaanchu quwi 1- 6 geeshsha woroonnihu agaramino gedeenni hee'reenna Zoonete woy Hawaasi quchumi gashshooti investimentete komite:
   a) Investimentete hossanno baatto xa'mantanno woyte baatto wole horora hossinokkita ikkasenna ayno yekkeeramannokkita ikkase buuxatenninna hornayase keenatenni seera agarino garinni qoqqowu mootimmara murote shiqishanno;
   b) Investimentete seeri garinni garunni loosantinokki pirojekituwara hasiisanno qaafo adhitanno; sheemate diigganno.

**GAFA ONTE**

**<u>ADDI ADDI WORO</u>**

**19. Baatto Afi'ranna Saysa**

1. Aye investere baadiyyete investimentete baatto afi'rara dandaannohu garimma noosi baadiyyete baatto gashshooti seeri garinniiti;
2. Quchumaho investimentete baatto afi'rara dandaannohu garimma noosi quchumu baatto saysate fulino liizete seeri garinni ikkanno;

6 ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናል፤

7 በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ – ፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን ወይም የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚቴ፡-

ሀ) ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት ሲጠየቅ መሬቱ ከማንኛውም ይዞታና ከሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት ነጻ መሆኑን በማረጋገጥ እና ፋይዳውን በመመዘን ተገቢውን ህግና ደንብ ተከትሎ ለክልሉ መንግስት ለውሳኔ ያቀርባል፤

ለ) የኢንቨስትመንት ህግና ደንብ ተከትሎ በአግባቡ በማያለሙ ፕሮጀክቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ ውል ይሰርዛል፡፡

**ክፍል አምስት**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**፲፱ መሬት ስለማግኘትና ስለማስተላለፍ**

1 ማንኛውም ባለሀብት በገጠር ለሚደረግ ኢንቨስትመንት መሬት ማግኘት የሚችለው አግባብ ባለው የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

2 በከተማ ለሚደረግ ኢንቨስትመንት መሬት የሚተላለፈው አግባብ ባለው የከተማ መሬት

3. Tenne wodhonni worroonniri noo gedeenni hee'reenna gashshootu taqqara investimentete baatto aamantanno gara albillite jeefisaanote amaale mini gumulanno.

**20. Koffeenya Shiqishi'ra**

1. Investimentete loossa jeefishshi aana koffi yiihu ayno koffeenya deerru deerrunkunni uurritino investimentete komitera shiqishanno;
2. Komitete dawaronni kassi yaa hoogiro kofeenyasi boordete shiqishira dandaanno.

**21. Halamate Gadacho**

1. Ayno qoqqowu mootimma jeefisiisanno bisi investimentete amadantino garimma noonsa tajubba komishiinete aatenni halamate gadadi noosi.
2. Komishiine investere riqibbe owaante gumulsiisate assitanno millimmo lifixanna gumaame assate qeechase garunni fula dandiitanno gede jeefisiisaano bissa halamate gadacho noonsa.

**22. Baajeettete Buicho**

Komishiinete baajeettete buicho:

1. Qoqqowu mootimmanni gaammanni baajeettenni;
2. Komishiine uytanno owaantenni gamba assinanni eonni ikkanno.

ለማስተላለፍ በወጣው የሊዝ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

3 በዚህ ደንብ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየአስተዳደር እርከኑ የኢንቨስትመንት መሬት የሚተላለፍበት ሁኔታ ወደ ፊት በመስተዳድር ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል፡፡

**፳ አቤቱታ ስለማቅረብ**

1 በኢንቨስትመንት ስራዎች አፈጻጸም ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን አቤቱታውን በየደረጃው ለተቋቋመ ኢንቨስትመንት ኮሚቴ ያቀርባል፤

2 ኮሚቴው በሚሰጥ ምላሽ ካልረካ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፳፩ የመተባበር ግዴታ**

1 ማንኛውም የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካል ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን ለኮሚሽኑ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2 ኮሚሽኑ ባለሃብቶችን ተክቶ አገልግሎቶችን ለማስፈጸም የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ፣ ኃላፊነቱን በአግባብ መወጣት እንዲችል አስፈጻሚ አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**፳፪ የበጀት ምንጭ**

የኮሚሽኑ የበጀት ምንጭ፡-

1 የክልሉ መንግሥት የሚመደበው በጀት፤

2 በሚሰጠው አገልግሎት ከሚሰበሰበው ገቢ ይሆናል፡፡

**23. Baajeettete Diro**

Komishiinennihu baajeettete diri qoqqowu mootimma baajeettete diro ikkanno.

**24. Shallagote Taje**

1. Komishiine wo'manna halaalaancho shallagote taje amadanno.
2. Komishiine shallagote tajenna woxe la'anno tajubba qoqqowu qara odiitere woy qara odiiterenni somantanno ogeeyyenni diru dirunni qorqorsha assitanno.

**25. Jeefishshu Nookki Seerubba**

Tenne wodho ledo kiphi yitanno aye wodhonna biddissi woy rosichu asooti tenne wodhonni hanqafantino hajubbara jeefishshu diheeranonsa.

**26. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Borde tenne wodho loosu aana hosiisate hasiissanno biddissubba fushshate dandiitanno.

**27. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho Maaja 1 barri 2012 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

**Hawaasa, Arfaasa 1, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

**፳፫ የበጀት ዓመት**

የኮሚሽኑ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግሥት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

**፳፬ የሒሳብ መዛግብት**

1 ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2 የኮሚሽኑ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በክልሉ ዋና ኦዲተር ወይም ኦዲተሩ በሚሰይመው ሌላ ኦዲተር እንደየአስፈላጊነቱ ይመረመራሉ፡፡

**፳፭ ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

**፳፮ መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ቦርዱ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፯ ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፩ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ፣ ጥር ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ደስታ ለዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**